# የታሪፍ ፖሊሲ

የመጓጓዣ ታሪፎች በአለም ዙሪያ ላሉ የጉዞ ድርጅቶች በጣም ጠቃሚ የገቢ ምንጭ ናቸው። በ Metro፣ የካውንቲ ህግ የገንዘባችን የተወሰነ ክፍል ከታሪፎች እንዲመጣ ያስገድዳል። ታሪፎች Metro የአሁኑን የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰጥ እና ወደ ፊት የመጓጓዣ ስርዓታችንን እንዲያሳድግ ይረዳሉ።

Metro የታሪፎች ዋጋ ሰዎችን በመጓጓዣ ከመጓዝ እንደማይከለክሉ ለማረጋገጥ ቁርጠኛ ነው።

# የታሪፎች የወደፊት ተነሳሽነት

Metro የታሪፍ ፕሮግራሞቻችንን የበለጠ ፍትሃዊ፣ ለመጠቀም ቀላል እና ለመስራት ቀላል እንዲሆን ለማድረግ፣ በ 2023-2026 ባለብዙ ክፍል **የታሪፎች የወደፊት ተነሳሽነትን** እያስጀመረ ነው።

የዚህ ተነሳሽነት አራት የፕሮጀክት ዘርፎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

1. Simplify Reduced Fare Programs (የተቀነሱ የታሪፍ ፕሮግራሞችን ማቅለል)

   Metro የተለያዩ የቅናሽ ታሪፍ ፕሮግራሞችን ያቀርባል፣ ነገር ግን ለደንበኞች አጠቃቀም ወይም ለሠራተኞች ሥራ ሁልጊዜ ቀላል አይደሉም። Metro ያንን ለመቀየር እየሰራ ነው።

   ከ 2023 ጀምሮ፣ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ተጓዦች እንደ ORCA LIFT ፕሮግራም፣ ለአረጋውያን እና ለአካል ጉዳተኛ ተጓዦች Regional Reduced Fare Permit (ክልላዊ የተቀነሰ የታሪፍ ፈቃድ)፣ ለአንዳንድ የመንግስት ፕሮግራሞች ተሳታፊዎች ድጎማ የተደረገለት አመታዊ ማለፊያ አማካኝነት ወረቀት እና Human Service Bus Ticket Program (የሰብዓዊ አገልግሎት የአውቶቡስ ትኬት ፕሮግራም) ያሉ አገልግሎት አቅራቢዎች እና የማህበረሰብ ቡድኖች ለደንበኞቻቸው የአውቶቡስ ትኬቶችን እንዲያገኙ የሚረዱ የተቀነሱ የታሪፍ ፕሮግራሞችን ለማሻሻል Metro ተጓዦችን፣ የሰብዓዊ አገልግሎት ድርጅቶችን፣ የመጓጓዣ አጋሮችን እና ሌሎችን በአንድ ላይ ያሰባስባል።

   ስለ ቅናሽ ዋጋ አማራጮች ተጨማሪ

2. የታሪፍ ክፍያ አማራጮችን ማዘመን

   Metro እና ሌሎች በክልሉ ውስጥ ያሉ የህዝብ ማመላለሻ ድርጅቶች የ ORCA ካርዶችን ለመግዛት፣ ለመጫን እና ለመጠቀም ቀላል ለማድረግ አዳዲስ መሳሪያዎችን እና ሌሎች የጥሬ ገንዘብ ያልሆኑ የመክፈያ ዘዴዎችን እያስተዋወቁ ነው። እነዚህ ማሻሻያዎች የተጓዦችን ገንዘብ ይቆጥባሉ እንዲሁም በተለያዩ ኤጀንሲዎች እና የመጓጓዣ አይነቶች መካከል ለመዘዋወር ቀላል ያደርገዋል።

   ለረጅም ጊዜ፣ Metro በአውቶቡሶች ላይ የጥሬ ገንዘብ ታሪፍ ክፍያን ለማስቀረት እየተሻሻለ ነው።

ከ 2023 ጀምሮ፣ Metro ለዚህ ጥሬ ገንዘብ አልባ ሽግግር እቅድ እና የጊዜ ሰሌዳ ለማዘጋጀት ከህብረተሰቡ ጋር ይሰራል። ጥሬ ገንዘብ እንደ አማራጭ ከመወገዱ በፊት ምን አይነት ቴክኖሎጂዎች፣ የማህበረሰብ ተደራሽነት፣ ሽርክናዎች እና ሌሎች መሳሪያዎች መዘጋጀት እንዳለባቸው ለማወቅ እንሰራለን— በዚያ መንገድ ገንዘብ ከፋዮች ከሌሎች ዘዴዎች ጋር ለመገናኘት ጊዜ ይኖራቸዋል።

3. የፋይናንስ ፖሊሲዎች ማዘመን

   የካውንቲ ህግ Metro የገንዘባችን የተወሰነ ክፍል ከመጓጓዣ ታሪፎች እንዲሰበስብ ያስገድዳል።

   ለ2025 ወረዳ የበጀት ሂደት፣ Metro ከሌሎች ውሂቦች በተጨማሪ፣ ወደፊት ምን ያህል ሰዎች ወደፊት በአውቶቡስ ይሳፈራሉ ብለን እንደምንጠብቅ ወቅታዊ ግምቶች ላይ በመሰረት በእነዚህ የህግ መስፈርቶች ላይ ለውጦችን ያቀርባል።

4. በ ORCA በኩል ትክክለኛ የታሪፍ ተደራሽነትን ማስፋፋት

   የ Metro ተሳፋሪዎች መጓጓዣ እንዲመርጡ ቀላል እና የበለጠ ተመጣጣኝ ለማድረግ ሁል ጊዜ ይሰራል።

   በሚቀጥሉት ጥቂት አመታት Metro በ ORCA በኩል ለተጓዦች ካርዶች መስጠት ላይ ትኩረት በማድረግ፣ ከማህበረሰብ አቀፍ ድርጅቶች ጋር በመተባበር እና የ ORCA ካርዶችን እንዲገዙ እና እንዲጭኑ የሚያስችልዎትን የችርቻሮ መደብሮች ብዛት በመጨመር ከትክክለኛው ታሪፍ ጋር ማገናኘቱን ይቀጥላል።

   [በአቅራቢያዎ ያለ የORCA ቸርቻሪ ያግኙ]

## የግብረመልስ እድሎች

በታሪፍ ስርዐታችን ላይ ሊደረጉ በሚችሉ ለውጦች ተጽዕኖ ያደረባቸው የማህበረሰቦችን ፍላጎቶችን እና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች የበለጠ ለመርዳት Metro የማህበረሰብ ግብዐትን ይፈልጋል።

*የታሪፍ ካቢኔ*

Metro በአዲስ የታሪፍ ፖሊሲዎች በጣም የተጎዱትን/ከዚህ ቀደም ከእንዲዚህ ባሉ አስፈላጊ ውይይቶች ያልተሳተፉ የማህበረሰብ አባላትን ያቀፈ የታሪፍ ካቢኔ ይፈጥራል።የ ካቢኔ አባላት ለ Metro የታሪፍ ፕሮጀክቶች እና ህዝቡን በተሻለ መንገድ ማግኘት በሚቻልባቸው መንገዶች ላይ ያላቸውን አስተያየት ይሰጣሉ።

በ 2024 ካቢኔው በመደበኛነት ይሰበሰባል፣ እና አባላት ለተሳትፏቸው እና ለአስተያየታቸው ክፍያ ይከፈላቸዋል።

**የ Metro የታሪፍ ካቢኔ አካል ይሁኑ!**

የታሪፍ ካቢኔ ለመሆን ለማመልከት የመጨረሻው ቀን ዲሴምበር 31፣ 2023 ነው።

[እዚህ ያመልክቱ]

[የMetro አማካሪ ቡድኖች]

*የክልል ቅንጅት*

እንዲሁም የMetro ታሪፎች የወደፊት ተነሳሽነት ስኬት በክልላችን የመጓጓዣ ድርጅት ውስጥ ባሉት አጋሮች ተሳትፎ ይወሰናል። ለዚህ ቅናሽ የታሪፎች ስራ፣ Metro ከአጋር ድርጅቶቻችን ተወካዮች ጋር ልዩ የፕሮጀክት ቡድን ያቋቁማል። እንዲሁም Metro ማሻሻያዎችን የሚያቀርብ ሲሆን ከአጋር የመጓጓዣ ድርጅቶች ተወካዮች በነባር ንዑስ ኮሚቴዎች እና ሌሎች የክልል ስብሰባዎች በኩል ግብዐት ይፈልጋል።

*ማህበረሰብ ተኮር የድርጅት ሽክናዎች*

Metro ቅድሚያ የሚሰጧቸውን ማህበረሰቦች Metro ን ወክለው ግብረ መልስ የሚጠይቁ ማህበረሰብ ተኮር ድርጅቶችን እንደ ስርጭት አጋሮች እንዲያገለግሉ ይቀጥራል። Metro ለእነዚህ ድርጅቶች ለባህላቸው እና ለደንበኞቻቸው ተስማሚ የሆነ የተሳትፎ ተግባራትን በማዘጋጀት እና በማከናወን ላይ ላዋሉት ችሎታ እና ጊዜ ይከፍላቸዋል።

*የአጋር ተሳትፎ*

Metro በፕሮጀክት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች እንዲገመግሙ እና አስተያየቶችን እንዲሰጡ የማህበረሰብ ድርጅቶች አባላትን ከታሪፍ ካቢኔ ይጋብዛል።

## የሚሉት ነገር ካለ

*እኛን ያግኙን*

እባክዎ በመረጡት ቋንቋ በኢሜይል ያግኙን፦ haveasay@kingcounty.gov

*አጠቃላይ አስተያየቶች*

ስለ Metro አገልግሎቶች አጠቃላይ አስተያየት ካለዎት፣ እባክዎን የእኛን የግብረ መልስ ቅጾችን ይጠቀሙ ወይም በ 206-553-3000 ይደውሉልን። የአስተርጓሚ አገልግሎቶች አሉ።

## ተዛማጅ ርዕሶች

*ታሪፎች እና ክፍያዎች*

ለጉዞዎ ለመክፈል ስለተለያዩ መንገዶች እና ስለአሁኑ ታሪፎቻችን የበለጠ ይወቁ።

*ቅናሽ ታሪፎች*

በ ORCA LIFT (አንድ ክልላዊ ካርድ ለሁሉም)፣ በ Regional Reduced Fare Permit (RRFP፣ ክልላዊ የተቀነሰ ታሪፍ ፈቃድ) እና በድጎማ ስለሚደረግ አመታዊ ማለፊያ የመጓጓዣ ታሪፎችን ስለመቆጠብ መንገዶች ይወቁ።

*ORCA ካርዶች*

የ ORCA ካርዱ የሚከፈልባቸው ታሪፎችን እና ዝውውሮችን በራስ ሰር ይከታተላል፣ ስለዚህ እርስዎ ማድረግ የለብዎትም።